ታህሣሥ 05 ቀን 2003 ዓ.ም

# በኢትዮጵያ ተጠልለው የሚገኙ ኤርትራዊያን ስደተኞች ወደ ሦስተኛ አገር ስለሚሄዱ ስሸኛኘታቸውን ስለመለከቶ የተሰጠ መግለጫ

የኤርትራ መንግስት በዜጎቹ ላይ እያደረሰ ባለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት የሚሰደዱ የኤርትራውያን ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በወር ከ2,000 በላይ ኤርትራዊያን ድንበር አቋርጠው እየመጡ ይገኛሉ:: ከእነዚህ ውስጥ 40% የኤርትራ ወታደሮች የነበሩ ናቸው::

የኢትዮጵያ መንግስት ለኤርትራ ስደተኞች አቅም በፈቀደ መጠን መልካም አቀባበልና አያያዝ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከድንበር አካባቢዎች አቀባበል ጀምሮ በኢትዮጵያ ባላቸው ቆይታ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን፣ በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ሰብአዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙ፣ በኢትዮጵያ በመረጧቸው ቦታዎች መኖር እንዲችሉና የከፍተኛ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ በያዝነው በ2003 ዓ.ም ላይ ብቻ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 118፣ በመቀሌ 70፣ በአክሱም 29 ስደተኛ ተማሪዎች ስመጀመሪያ ዲግሪ፣ 5 ተማሪዎች በሁለተኛ ዲግሪ፣ በድምሩ 294 ስደተኛ ተማሪዎች እየተማሩ የሚገኙ ሲሆን በሠመራ ዩኒቨርስቲ 62 ተማሪዎች ለማስተማር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል::

በተጨማሪም የተለያዩ አገራት ለኤርትራዊያን ስደተኞች ዘላቂ መፍትሄ ከመስጠት አኳያ የሪሴትልመንት ዕድል በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በዚህም እ.ኤ.አ ከ2006 - 2009 ድረስ ብቻ 5,822 ኤርትራዊያን ወደ ተለያዩ አገሮች በሪሴትልመንት ሄደዋል::

በያዝነው የፈረንጆች 2010 ዓመት በተያዘው እቅድ መሠረት 3,100 ስደተኞችን ለመላክ ታቅዶ የዛሬዎቹን ጨምሮ 2,847 ኤርትራዊያን ስደተኞች በሪሴትልመንት ወደ ሦስተኛ አገር የተጓጓዙ ሲሆን፤ በዛሬው ዕለትም 61 ኤርትራዊያን ወደ አሜሪካ ተሸኝተዋል:: በዚህ መሰረት ለአመቱ የተያዘው ስደተኞችን በሪሴትልመንት የማጓጓዝ እቅድ 90% ተከናውኗል::

በአሁኑ ሰዓትም በአምስት መጠለያ ጣቢያዎች 53,767 ኤርትራውያን ስደተኞች በትግራይ ክልል በሽመልባ፣ ማይዓይኒና አዲሐሩሽ፣ በአፋር ክልል በአሳኢታና በበራሕሌ እንዲሁም በተለያዩ ከተሞች ተጠልለው ይገኛሉ::

በዛሬው ዕለት የተሸኙትንም ስደተኞች በስደተኞች ጉዳይ አስተዳደር አሸኛኘት ተደርጎላቸው ወደ አሜሪካ የሄዱ ሲሆን ስደተኞቹን የማጓጓዝ ሥራ ከUNHCR እና ከIOM ጋር በመተባበር እየተከናወነ ይገኛል::

**የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር**